የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ (ኢፖእአኮ)
SOLIDARITY COMMITTEE FOR ETHIOPIAN
POLITICAL PRISONERS (SOCEPP)

መስከረም 1/2004

# የአዲስ ዓመት እንኳን አደረሳችሁ የፖለቲካ እስረኞችን አይዘንጋ

የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ ለአባሎቹ፤ደጋፊዎቹና መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ መልካም አዲስ ዓመት ይሁንላችሁ እያለ ዜጎች በሞላ ለህገረና ወገን ብለው በመታገላቸው ለእስርና ስቃይ ተዳርገው ያሉ ወገኖቻችን እናስታውሳቸው፤ እንዲለቀቁም እንታገልላቸው ይላል።

ኢፖእአኮ በወያኔ ማጎሪያዎች እየተሰቃዩ ያሉትን ከ 35 ሺ በላይ ወገኖች፤ ደብዛቸው የጠፋውን ብዙዎችን፤ ስየል እየተቀበሉ ያሉትን ሁሉ ማስታወስና እነሱና ቤተሰቦቻቸው አዲሱ ዓመት መልካም እንደማይሆንላቸው ማወቅ ይኖርብናል። ስቃይናና መከራ ነው 2004 ይዞላቸው የመጣውና። ለሀገርና ወገን ብለው ራሳቸውን ለጥቃትና መከራ ያጋለጡትን ወገኖችና በየማጎሪያው የሚሰቃዩትን፤ በየምስጢር እስር ቤቶች መከራ የሚቀበሉትን፤ ለዓመታት ደብዛቸው የጠፋውን ዜጎች ሁሉ ማስታወስና ይህን ግፍ የፈፀመውን አገዛዝ ለማጋለጥና ለማውገዝ ቆርጠን መነሳት ይጠበቅብናል።

የምን ዕንቁጣጣሽ የማጎሪያ ቤቶች ሁላቸው ሳይወድሙ
የምን ዕንቁጣጣሽ የታፈኑ ዜጎች ከጉድጓድ ሳይወጡ
የምን አዲስ ዓመት ግፉ እየቀጠለ
መከራው ሰቆቃው አላባራ እያለ
የምን ዕንቁጣጣሽ መብታቸን ታፍኖ
ስንቱ ሺ ወገናችን ታፍኖ ታግሮ።

ተብሏልና ኢፖእአኮ ሁሉም ሀገር ወዳድ ዜጋ መልካም አዲሰ ዓመት ሲባባል የታሰሩትና በወያኔ እየተሰቃዩ ያሉትን ዜጎች እንዲያስታውስ፣ሰማዕትን እንዲዘክርና ለመብት መከበርም እንዲታገል ጥሪ ያደርጋል። ግፍና በደሉ ከቀጠለ ዓመቱ አዲስ አይሆንም። ወገኖቻችን በየማጎሪያው መከራና ፍዳ መቀበል ከተቀጠሉ ዓመቱ አዲሰ ሳይሆን ያው የኖርነው የመከራ ዓመት ቀጣይ ይሆናል።

በቅርቡ አርቲስት ደበበ እሸቱን ጨምሮ ወደ 30 የሚጠጉ ዜጎች  በአፋኙ ና ህገወጡ ፀረ ሽብርተኛ ተ ብዬ ድንጋጌ ሽፋን ታስረዋል:: የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በአፈናውና ግፉ ቀጠለ እንጂ አደብ አልገዛም፤ አ ልተሻሻለም:: ይህም በመጪው ዓመት ቆርጠንና ተጠናክረን ለሰበዓዊ መብት መከበር መታገል እንዳለ ብን
ጠቋሚ ነው::

መጪው ዓመት የነፃነትና የዴሞክራሲ ትግሉ ድል የሚታይበት ይሆን ዘንድ በጋራ ለሰብዓዊ መብት መከበር እንታገል::

INJUSTICE ANYWHERE IS INJUSTICE EVERYWHERE
SOCEPP, POSTFACH 51213, BERLIN 13372,GERMANY
SOCEPP, 30 RIGA COVE, WINNIPEG,MB R2P 2Z7,CANADA
E MAIL: SOCEPP @AOL.COM
WEB SITE: WWW.SOCEPP.DE